አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ.

LION INTERNATIONAL BANK S.C.

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የጥቆማ እና የምርጫ አፈጻጸም ፖሊሲ እና መመሪያ

አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ.

ሀዳር 2017 ዓ.ም

መግቢያ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣቸው የባንኮች ተቋማዊ አስተዳደር መመሪያ (Bank Corporate Governance Directive) ቁጥር SBB/91/2024 እና በባንክ ውስጥ ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰዎች ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶች መመሪያ (Requirements for persons with significant influence in a bank Directive) ቁጥር SBB/89/2024 መሠረት ባንኮች የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ እና ሹመት ሂደትን ለመቆጣጠር ከመመሪያዎቹ የመነጨ ፖሊሲ እና የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ ማውጣት እንዳለባቸው ተደንግጓል።

በዚሁ መሰረት ጉባኤው ከዚህ ቀደም ይገለገልበት የነበረው የአስመራጭ ኮሚቴ መመሪያ ተሽሮ አዲስ የቦርድ አባላት የጥቆማ እና የምርጫ አፈጻጸም ፖሊሲ እና መመሪያ ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ ማስፀደቅ በማስፈለጉ ይህን መመሪያ ለተከበረው ጉባኤ ውይይት ቀርቧል።

ስያሜ

"የአንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የጥቆማ እና የምርጫ አፈጻጸም ፖሊሲ እና መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

ዓላማ

በባንኩ ውስጥ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚያስችል ግልፅነትን የተላበሰ፣ እንዲሁም የብሄራዊ ባንክና ሌሎች ተገቢነት ያላቸው መመርያዎች ባገናዘበ መልክ የዳይሬክተሮች የትምህርት ዝግጅት፣ የሥራ ልምድ፣ የአመራር ክህሎት፣ የያታ ተዋፅያና ስብጥር ያስጠበቀ የዳይሬክተሮች ምርጫ ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት ነው።

ትርጓሜ

ሀ. "ተፅዕኖ ፈጣሪ ባለአክስዮን" ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከባንኩ የተፈረመ ካፒታል 2%/ሁለት ከመቶ/ እና ከዛ በላይ የሆነ የባንኩ የተፈረመ ካፒታል የያዘ (ባለ ድርሻ) የሆነ ሰው ነው፡

ለ. "ተፅዕኖ ፈጣሪ ያልሆነ ባለአክስዮን" ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከባንኩ የተፈረመ ካፒታል ከ2%/ሁለት ከመቶ/ ያነሰ የባንኩ የተፈረመ ካፒታል የያዘ ባለ ድርሻ የሆነ ሰው ነው፡

ሐ. "የጥቆማ እና የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ" ወይም "አስመራጭ ኮሚቴ" ማለት በጉባኤ ዕለት በባለአክስዮኖች የሚሰየም የዳይሬክተሮች የጥቆማ እና የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ ነው።

Documents Registration Service
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
10

መ."ገለልተኛ ዳይሬክተር" የባንኩ ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ያልሆነ፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከባንኩ ዳይሬክተሮች፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ወይም ሲንየር ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከነዚህ አካላት ጋር የመጀመሪያ ደረጃ የጋብቻ ወይም የዝምድ እና የቤተሰብ ወይም የንግድ ሥራ፣ ሙያዊ ወይም የንግድ ግንኙነት የሌለው፤ ወይም በባንኩ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ የሌለው ዳይሬክተር ማለት ነው።

ቀጥሎ የተዘረዘሩት የተፈጥሮ ሰዎች ገለልተኛ ዳይሬክተር ተደርገው አይቆጠሩም፡-

i. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የባንኩ ባለአክስዮን፣ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ወይም ሲንየር ሥራ አስፈጻሚ የሆነ እና/ወይም ከነዚህ አካላት ጋር የመጀመሪያ ደረጃ የጋብቻ ወይም የዝምድና ግንኙነት ያለው፤ ወይም

ii. ከባንኩ ጋር የውል ግዴታ ባለቤት ኩባንያ ውስጥ ባለአክስዮን፣ ዳይሬክተር፣ ዋና ስራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ስራ አስፈፃሚ የሆነ፤

iii. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከባንኩ፣ ባንኩ ከሚያስተዳድራቸው ድርጅቶች እና ከአጋር ድርጅቶች ጋር በፍርድ ቤት የሕግ ክርክር ያለው፣ ወይም ከፍርድ ቤት ውጪ የሆነ ግጭት እና አለመግባባት ያለው፤

iv. ባለፉት ሁለት ዓመታት ከባንኩ ጋር የቢዝነስ፣ የሙያ ወይም የንግድ ግንኙነት ያለው፤ እና

v. በባንኩ ላይ በድምሩ የብር ሐምሳ (50) ሚልዮን የሚደርስ የገንዘብ ነክ (የፋይናንሻል) ግዴታ ያለበት።

ሠ. "አንድ የአገልግሎት ዘመን" ማለት ከሦስት (3) ዓመት ያልበለጠ የአገልግሎት ዘመን ነው።

ክፍል ሁለት
አጠቃላይ ፖሊሲዎች

2. ፖሊሲዎች

2.1. የባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ

- የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የባንኩ ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካል ነው። በዚሁ መሰረት ባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ፡-
  - የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ሹመት ፖሊሲ እና የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ ያፀድቃል፤
  - በጉባኤው ዕለት የጥቆማ እና ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይመርጣል፤
  - የብሔራዊ ባንክን መስፈርቶች የሚያሟሉ፣ በባንኩ ላይ እሴት የሚጨምሩ ብቁ እና ታማኝ ሰዎች ዳይሬክተር እንዲሾሙ በቅን ልቦና ይሰራል፤
  - የዳይሬክተሮች ጥቆማ እና ምርጫ ያከናውናል፤
  - በምርጫው ከየምድቡ አብላጫ ውጤት በማግኘት ያሸነፉትን ዕጩዎችን ስም ዝርዝር ከነተጠባባቂያቸው በቃለ ጉባኤ ያፀድቃል።

2.2. የጉባኤ ድምፅ ቆጣሪዎች

- ጉባኤው ወደ መደበኛ ስራው ከመግባቱ አስቀድሞ ምልአተ ጉባኤውን የሚያረጋግጡ እና በጉባኤው ውስጥ ከድምፅ ቆጠራ ጋር የተያያዙ ስራዎችን የሚከውኑ ድምፅ ቆጣሪዎች ፈቃደኛ ከሆኑ ከፍተኛ ባለአክስዮኖች መካከል በሚደረግ ስምምነት ይሰየማሉ።
- በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት የድምፅ ቆጣሪ መሆን የሚችሉት ባለአክስዮኖች ፈቃደኛ ካልሆኑ ወይም በጉባዔው የተገኙት ባለአክስዮኖች ሌላ ሰው መምረጥ ከፈለጉ ስብሰባው እንደተጀመረ የድምፅ ቆጠራውን ለማድረግ የሚያስፈልጉ ድምፅ ቆጣሪዎችን መምረጥ አለባቸው።
- በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) እና (2) የተደነገገው ቢኖርም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚደረግ ስብሰባን ድምፅ ለመቁጠር አስተማማኝ የሆነ የድምፅ ቆጠራ ለማድረግ የሚያስችል ቴክኖሎጂን መጠቀም ይቻላል።

2.3. በጠቅላላ ጉባኤ ላይ በውክልና ስለሚደረግ ተሳትፎ

- በውክልና ድምፅ የመስጠት ባለአክስዮች የራሳቸውን ጨምሮ ሊይዙት የሚገባ አጠቃላይ ድምፅ ከባንኩ የተመዘገቡ ፈርጅታል ከአስር በመቶ (10%) መብለጥ የለበትም፤

Documents Authentication and Registration Service Bureau
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
10

- ማንኛውም የባንኩ የቦርድ አባል፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና ሲንየር ሥራ አስፈጻሚ፣ እንዲሁም ሰራተኛ በባንኩ የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የሌላ ባለአክስዮን ተወካይ መሆን አይችልም (ባለአክስዮኖችን ወክሎ ድምፅ መስጠት አይችልም)

2.4. ባለአክስዮኖች ወደ ምርጫ ከመግባታቸው በፊት ሊያገኙት ስለሚገባ መረጃ

- የማህበሩ ፀሐፊ የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ከመካሄዱ ከአንድ ወር አስቀድሞ የቦርድ አባላት የጥቆማ እና ምርጫ መስፈርቶችን እንዲሁም ዕጩዎችን በመጠቆም እና በመምረጥ ሂደት ሊከተሏቸው የሚገቡ አሰራሮችን የተመለከተ መረጃ ተደራሽነት ባላቸው አግበቦች ሊያገኙ ይገባል።
- በጉባኤው የሚመረጥ አስመራጭ ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀውን የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ ለንባብ በሚያመች መንገድ ተስተካክሎ ሊሰጠው ይገባል፤
- የማህበሩ ፀሐፊ ለምርጫው ሂደት የሚያስፈልጉ የዕጩዎችን ምድብ በቀላሉ ለመለየት በሚያስችሉ ሦስት ዓይነት ቀለማት የተለዩ የድምፅ መስጫ ካርዶች፣ የድምፅ መቀበያ ሳጥኖች እና የኦድዮ-ቪዥዋል ግብአቶች፤ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶች መዘጋጀታቸውን ያረጋግጣል።

2.5. የቦርድ የሹመት እና የክፍያ ጉዳዮች ኮሚቴ

- በዚሁ መመሪያ መሰረት ብቃት ያላቸው ገለልተኛ ዕጩዎችን በመመልመል ከአጭር የግለታሪክ መግለጫ ጭምር ለዳይሬክተሮች ቦርድ ውይይት በማቅረብ ያስጸድቃል፤
- በዳይሬክተሮች ቦርድ ተቀባይነት ያገኙ ገለልተኛ ዕጩዎች ስም ዝርዝር እና ተያያዥ መረጃ ለጥቆማ እና ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴው በማስረከብ ለቦርድ አባላት ምርጫ ያቀርባል፤
- ኮሚቴው ለምርጫ የሚያቀርባቸው ዕጩዎች ቢያንስ የብሔራዊ ባንክ ዝቅተኛ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤ እንዳስፈላጊነቱም ለጉባኤው ስለዕጩዎቹ ዝርዝር መረጃ በመስጠት ለድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል።

2.6. በጉባኤ የሚደረግ የጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ አሰያየም

- ምርጫ በሚደረግበት ጉባኤ ላይ 5 አባላት ያሉት የአስመራጭ ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባኤው ምርጫ ይሰየማል።
- ከኮሚቴው አባላት መካከል ቢያንስ ሁለቱ (2) ተፅዕኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክስዮኖች መሆን አለባቸው።

- ኮሚቴው በስራ ላይ ያሉትን የቦርድ አባላት እና የባንኩ ሰራተኞችን በውስጡ አያካትትም፤
- የተሰየመው አስመራጭ ኮሚቴ በዕለቱ የዕጩዎች ጥቆማ የመቀበል እና ምርጫን የማካሂድ ኃላፊነት አለበት።

2.7. የዳይሬክተሮች ቦርድ አወቃቀር እና ስብጥር

- ለውድድር የሚቀርቡ ተጠቋሚ ዕጩዎች ቁጥር በጠቅላላ ጉባኤው የሚወሰን ሲሆን፤ የዕጩዎች ቁጥር በባንኩ ከተወሰነው የቦርድ አባላት መቀመጫ ቁጥር ከዕጥፍ ማነስ የለበትም፤
- የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚዋቀረው ቀጥሎ በተዘረዘረው አወቃቀር እና ስብጥር መሰረት ይሆናል፡-
    - ከቦርዱ አጠቃላይ መቀመጫ 1/3ኛው ተዕዕኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክስዮኖች የሚጠቆሙ እና የሚመረጡ ይሆናል፤
    - ሌላው 1/3ኛው በሁሉም ባለአክስዮኖች የሚጠቆሙ እና የሚመረጡ ይሆናል፤ እንዲሁም
    - ቀሪው 1/3ኛው ገለልተኛ ዳይሬክተሮች ደግሞ በስራ ላይ ባለው ቦርድ ተጠቁመው በሁሉም ባለአክስዮኖች በጋራ የሚመረጡ ይሆናል።
- በቦርድ ውስጥ ቢያንስ ሁለት (2) ሴቶች በቦርድ አባልነት መመረጥ አለባቸው።
- የባንኩ የማህበሩ ፀሀፊን ሳይጨምር ዋና ሥራ አስፈፃሚውን እና ሲንየር ሥራ አስፈፃሚን ጨምሮ ቢበዛ ሁለት (2) ሰራተኞች ለቦርድ አባልነት ሊጠቆሙ እና ሊመረጡ ይችላሉ።
- ህጋዊ ሰውነት ያለው ማንኛውም አካል ለቦርድ አባልነት በዕጩነት መጠቆም እና መመረጥ ይችላል።
- የሕግ ሰውነት ያለው አካል በሚጠቆምበት ወቅት ሕጋዊ ተወካዩ ለዳይሬክተርነት የሚያበቁ መስፈርቶችን የሚያሟላ ስለመሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል።

2.8. ዕጩ ለመሆን የሚያበቁ መስፈርቶች

- ከባለአክስዮኖች መካከል ዳይሬክተር ሆኖ የሚቀርብ ዕጩ:-
    - ምርጫው ከመደረጉ በፊት ቢያንስ ለሁለት ተከታታይ ዓመታት በባንኩ የተመዘገበ ባለአክስዮን መሆን አለበት።

Documents Authentication Service Branch
Registration
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
10

- ዝቅተኛውን የብሔራዊ ባንክ የትምህርት ዝግጅት፣ ብቃትና የሥራ ልምድ መስፈርት ማሟላት አለበት።
- ቦርዱ እንደ ቡድን የክህሎት፣ የሙያ እና የልምድ ብዝሃነት ያለው እንዲሆን ከማስቻል አኳያ ዕጩዎች በባንክ፣ በፋይናንስ፣ በሒሳብ አያያዝ፣ አስተዳደር፣ ኢኮኖሚክስ፣ የሕግ፣ የንግድ አስተዳደር፣ ኦዲቲንግ፣ የመረጃ ቴክኖሎጂ፣ የኢንቨስትመንት አስተዳደር እና ዘላቂነት ጋር የተያያዘ ዕውቀትና ልምድ ሊኖራቸው ይገባል።
- ከላይ ከተዘረዘሩት የትምህርትና ስልጠና መስኮች ከታወቀ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ እና አግባብ የሰባት (7) ዓመታት የሥራ ልምድ ሊኖረው ይገባል።
- ከአራት በላይ በሆኑ ሌሎች ድርጅቶች በቦርድ አባልነት በማገልገል ላይ የሚገኝ መሆን የለበትም።
- ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል በዕጩነት የተጠቆመ እንደሆነ ይኸው ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል የሚወክለው የተፈጥሮ ሰው ከላይ የተጠቀሱት መስፈርቶች ማማላት ይኖርበታል።

2.9. ገለልተኛ ዳይሬክተር ሆኖ የሚቀርብ ዕጩ

- ገለልተኛ ዳይሬክተር የባንኩ ባለአክስዮን መሆን የለበትም።
- በዜግነት ኢትዮጵያዊ ሆኑ ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ ሰዎች ገለልተኛ ዳይሬክተር ሆነው እንዲያገለግሉ ሊመረጡ ይችላሉ።
- ከላይ የተዘረዘሩት የትምህርት ዝግጅት መስፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅበታል። ቢያንስ የማስተማር ዲግሪ ሊኖረውና በማማከር፣ ወይም በኦዲት፣ ወይም በአደጋ ስጋት አስተዳደር፣ ወይም በማናቸውም አግባብነት ባላቸው የሥራ ዘርፎች ቢያንስ የአሥር (10) ዓመት የሙያ ልምድ ሊኖረው ይገባል።
- ገለልተኛ ዳይሬክተር በዕጩነት መቅረብ የሚችለው በስራ ላይ ባለው የቦርድ የሹመት እና ክፍያ ጉዳዮች ኮሚቴ ተመልምሎ በዋናው ቦርድ ተቀባይነት ሲያገኝ እና ስሙ ከአስፈላጊ መረጃዎች ጋር ለጥቆማ እና አስመራጭ ኮሚቴው ሲተላለፍ ነው።

2.10. ታማኝነት (Integrity)

➢ በብሔራዊ ባንክ የተቋማዊ አስተዳደር መመሪያ እና በዚሁ ፖሊሲና መመሪያ የተቀመጡ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማ እና ምርጫ ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ለውድድር የሚቀርብ ማንኛውም ዕጩ ዳይሬክተር ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ታማኝነት ባህሪያት ሊኖሩት ይገባል፡-

- ለባንኩ ታማኝ፣ የተከበረ እና ቅንነት

- በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር በማንኛውም የወንጀል ድርጊት ያልተከሰሰ እና የጥፋተኝነት ታሪክ የሌለው መሆኑ፤
- እራሱ ወይም እሱ የሚቆጣጠረው ጉልህ ተፅዕኖ የሚፈጥር ማንኛውም የቢዝነስ (የመንግስትም ሆነ የግል) ተቋም ከእምነት ማጉደል፣ ከማጭበርበር እና ከሌሎች የፋይናንሻል ወንጀሎች ጋር በተያያዘ ተጠርጥሮ በተቆጣጣሪ አካል ወይም ሙያዊ ምርመራ ለማድረግ ስልጣን ባለው አካል ምርመራ ያልተደረገበት እና ማስጠንቀቅያ ያልተሰጠው፣ እንዲሁም በመደበኛ ወይም በልዩ ፍርድ ቤት ያልተቀጣ፣ ዕግድ ያልተጣለበት ወይም ተግሣጽ/ወቀሳ ያልተሰጠው፤
- የባንኩ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ የሥራ አስፈፃሚ ከሆነም በቅርብ ጊዜ ውስጥ በባንኩ የተወሰደበት የዲሲፕሊን እርምጃ ሪከርድ የሌለው፤ ወይም በሰራተኛ ማስተዳርያ አዋጅ መሰረት ቅጣት ሊያሰጥ የሚችል የስነ-ምግባር ደንብ ጥሰት ያልፈጸመ፣

ክፍል ሦስት

ስልጣንና ኃላፊነት

3.1. የባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ

3.1.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ሹመት ፖሊሲ እና የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ ያፀድቃል፤

3.1.2. በጉባኤው ዕለት የጥቆማ እና አስመራጭ ኮሚቴ ይመርጣል፤

3.1.3. የብሔራዊ ባንክን መስፈርቶች የሚያሟሉ ዕጩዎችን ይጠቁማል፣ ድምፅ በመስጠትም ይመርጣል።

3.1.4. በምርጫው ከየምድቡ አብላጫ ውጤት በማግኘት ያሸነፉትን ዕጩዎችን ስም ዝርዝር ከእነ ተጠባባቂያቸው በቃለ ጉባኤ ያፀድቃል።

3.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣንና ኃላፊነት

3.2.1. በስራ ላይ ያለው ቦርድ የሚከተሉት ስልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

3.2.1.1. ለምርጫው የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶች አስቀድመው እንዲከወኑ ያደርጋል ስለመከወናቸውም ያረጋግጣል፤

3.2.1.2. የጠቅላላ ጉባኤው አጀንዳ ሲያዝ የአስመራጭ ኮሚቴ ምርጫ ስለመኖሩ በቀዳሚ አጀንዳነት እንዲያዝ ያደርጋል፣

3.2.1.3. ባለአክስዮኖች በዕጩዎች ጥቆማ፣ ምርጫ እና ድምፅ አሰጣጥ ሂደት ሊከተሏቸው የሚገቡ አሰራሮችንና ሂደቶችን በተመለከተ ለጉባኤው ዝርዝር መረጃ ይሰጣል።

3.2.1.4. በጉባኤው ከተገኙ ባለአክስዮኖች መካከል የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ምርጫ ሂደትን ይመራል፤ ያስመርጣል፣

3.2.1.5. አስመራጭ ኮሚቴው ካስመረጠ በኋላ መድረኩን ለኮሚቴው ያስረክባል፤

3.2.1.6. ኮሚቴው ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

3.3. የድምፅ ቆጣሪዎች ኃላፊነት

3.3.1.1. ጉባኤውን በይፋ ለመጀመር የሚያስችል ምልአተ ጉባኤ መሟላቱን ያረጋግጣሉ።

3.3.1.2. ጉባኤው ድምፅ በሚሰጥባቸው ውሳኔዎች ላይ የድምፅ ቆጠራ ያደርጋሉ።

3.3.1.3. በመራጮች የተሰጠን ድምፅ ከአስመራጭ ኮሚቴ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የድምፅ ቆጠራ በማካሄድ የጨረሱን ትክክለኛነት ያረጋግጣሉ።

3.4. የአስመራጭ ኮሚቴ ስልጣንና ኃላፊነት

3.4.1. የኮሚቴውን ሊቀ-መንበር እና ፀሐፊ በመምረጥ የጥቆማ እና የምርጫ ሂደቱን ይመራል፤

3.4.2. በህጉ መሰረት ከየምድቡ የዕጩዎች ጥቆማ ይቀበላል፤

3.4.3. በየምድቡ ሴቶች በዕጩነት መካተታቸውን ያረጋግጣል፤

3.4.4. ወደ ቀጣዩ የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ከመገባቱ በፊት የድምፅ መስጫ ካርዶች፣ የድምፅ መቀበያ ሳጥኖች፣ እና ለድምፅ ቆጠራ የሚያገለግል ሲስተም ዝግጁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

3.4.5. የድምፅ አሰጣጡ ምስጢራዊ በሆነ መንገድ እንዲከናወን ያደርጋል፤ የድምፅ ቆጠራ ያካሂዳል፤

3.4.6. የዳይሬክተሮች ቦርድ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ምርጫም ሆነ የዳይሬክተሮች ሹመት ግልፅነትና ተአማኒነት ባለው አኳኋን መካሄዱን፤ እንዲሁም በሀገሪቱ ህግና በዚህ ደንብ መሰረት መከናወኑን በማረጋገጥ የድምፅ ቆጠራ ውጤቱን ለጉባኤው በይፋ ያሳውቃል፤

3.4.7. የአስመራጭ ኮሚቴ አባል የዳይሬክተሮች ቦርድ ተጠቋሚ ዕጩ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፡፡

ክፍል አራት

ዝርዝር የጥቆማ አቀባበል እና የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ

4.1. የዕጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማ አቀባበል ሂደት

4.1.1. ቦርዱ ላሉት 11 መቀመጫዎች ቢያንስ ዕጥፍ ቁጥር ያላቸው (22) ዕጩዎች በጥቆማ ይቀበላል፤

4.1.2. ጊዚያዊ የቦርድ ጥቆማ እና ኮሚቴው በጥቆማ የሚቀበላቸው ዕጩዎች በሚከተሉት ሦስት ምድቦች ተከፍለው የተጠቆሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡-

ሀ. ምድብ 1 - ከጠቅላላው 1/3ኛ (ወይም 8) ዕጩዎች ተፅዕኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክስዮኖች ብቻ የተጠቆሙ፤

ለ. ምድብ 2 - ከጠቅላላው 1/3ኛ (ወይም 8) ዕጩዎች በሁሉም ባለአክስዮኖች (ተፅዕኖ ፈጣሪ በሆኑ እና ባልሆኑ ባለአክስዮኖች) የተጠቆሙ፤

ሐ. ምድብ ሦስት - ከጠቅላለው 1/3ኛ (ወይም 6) ዕጩዎች በስራ ላይ ባለው ቦርድ ጥቆማ የሚቀርቡ ገለልተኛ ዕጩዎች መሆናቸውን የረጋግጣል።

Documents Authentication & Registration Service Branch
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

4.1.3. ዋና ሥራ አስፈፃሚውን ጨምሮ የባንኩ ሰራተኞች በዕጩነት ለውድድር መቅረብ የሚችሉት በምድብ አንድ ወይም በምድብ ሁለት በባለአክስዮኖች ሲጠቆሙ ነው።

4.1.4. የፆታ ስብጥርን ለማስጠበቅ ከዕጩዎቹ መካከል ቢያንስ አራት (4) ሴቶች በጥቆማ መቅረባቸውን ያረጋግጣል፤

4.1.5. ባለአክስዮኖች ጥቆማ ሲሰጡ የዕጩዉን የትምህርት ዝግጅት፣ የሙያ ብቃትና የስራ ልምድ የተመለከተ አጭር መግለጫ መስጠት አለባቸው። በተጨማሪም የትኛው ባለአክስዮን የትኛውን ዕጩ እየጠቆመ እንደሆነ በግልፅ መታወቅ አለበት።

4.1.6. ባለአክስዮን እራሱን ለዕጩነት መጠቆም ይችላል።

4.1.7. ጊዚያዊ የቦርድ ጥቆማ እና አስመራጭ ኮሚቴው በጥቆማ የተቀበላቸውን የዕጩ ተመርጠው ለማገልገል ፈቃደኛ መሆናቸውን በጉባኤው ፊት ጠይቆ ያረጋግጣል፤ ፈቃደኝነታቸው ሲረጋገጥ ከየምድቡ እያንዳንዱ ዕጩ ቀጥሎ በተዘረዘሩት መሰረት በአጭሩ ራሱን ለጉባኤው እንዲያስተዋውቅ ዕድል ይሰጣል፤ በዚሁ መሰረት፤-

ሀ. ሙሉ ስሙንና ዕድሜውን፣

ለ. የትምህርት ደረጃውን እና የሰለጠነበት የሙያ መስክ፣

ሐ. የስራ ልምዱንና በኃላፊነት ያገለገለባቸው የስራ ዘርፎች፣

መ. ከታማኝነት ጋር የተያያዘ የህግ ተጠያቂነት ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ አጋጥሞት ከነበረ፣

ሠ. በጊዜው በሌሎች ተቋማት በዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ወይም በማገልገል ላይ ከሆነ የተቋማቱ ሰም እና ብዛታቸውን ይገልጻል።

4.1.8. በዕጩነት የተጠቆመ ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል የሚወክለውን የተፈጥሮ ሰው ለጉባኤው ያሳውቃል። ተወካዩም ከላይ በተጠቀሰው መሰረት ራሱን ለጉባኤው እንዲያሳውቅ ይደረጋል።

4.1.9. በጥቆማው ወቅት የተወካዩ ማንነት ማሳወቅ ያልተቻለበት ሁኔታ ከተፈጠረ ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል በሂደት የብሔራዊ ባንክን መስፈርት የሚያሟላ ተወካይ ይመድባል።

4.1.10. በጥቆማው ሂደት አስመራጭ ኮሚቴው ዕጩ ተጠቋሚዎችን አስመልክቶ የሚሰጣቸው አስተያየቶች እና ሐሳቦች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እና በሌሎች የሀገሪቱ ሕጐች ከተቀመጡ መስፈርቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት።

4.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ የድምፅ መስጫ ካርዶች

4.2.1. በምዝገባ ወቅት በቀላሉ ለመለየት እንዲያስችል ሦስት (3) ዓይነት ቀለም ያላቸው የድምፅ መስጫ ካርዶችን ለጉባኤው ተሳታፊዎች ይሰጣል፤ አንደኛው ተፅዕኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክስዮኖች ብቻ ድምፅ የሚሰጡበት፤ ሁለተኛው በስራ ላይ ባለው ቦርድ ለተጠቆሙ ገለልተኛ ዕጩዎች በሁሉም ባለአክስዮኖች ድምፅ የሚሰጥበት፤ ሦስተኛው ደግሞ በሁሉም ባለአክስዮኖች ለተጠቆሙ ዕጩዎች ድምፅ የሚሰጥበት ይሆናል፤

4.2.2. የድምጽ መስጫ ካርዶች ለባለአክስዮኖች በዕለቱ የስብሰባ መዝገብ /አቴንዳንስ/ በሚፈርሙበት ጊዜ ይሰጣል፡፡

4.3. የድምጽ አሰጣጥ እና ቆጠራ ሥነ ሥርዓት

4.3.1. አስመራጭ ኮሚቴው የምርጫውን ሂደት ቆጠራውን ጨምሮ በቅርበት ይከታታላል፤

4.3.2. የዕጩዎችን ዝርዝር በሶስት (3) ምድቦች ከፋፍሎ በማዘጋጀት ለየምድቡ በተዘጋጀው የድምፅ መስጫ ካርድ ላይ በሚከተለው ቅደም ተከተል መሰረት ድምፅ ያሰጣል፡-

4.3.2.1. መጀመሪያ ተፅዕኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክስዮኖች ብቻ በሚመረጡ 1/3ኛ (8) ዕጩዎች ላይ ድምፅ ያሰጣል፣

4.3.2.2. በመቀጠል በሁሉም ባለአክስዮኖች የሚመረጡ 1/3ኛ (8) ዕጩዎች ላይ ድምፅ ላይ ያሰጣል፣

4.3.2.3. በመጨረሻም ገለልተኛ ለሆኑ ዳይሬክተሮች በሁሉም ባለአክስዮኖች የሚመረጡ 1/3ኛ (6) ዕጩዎች ላይ ድምፅ ያሰጣል።

4.3.3. የድምጽ ቆጠራው ሲጠናቀቅ አስመራጭ ኮሚቴው የድምጽ አሰጣጥ እና ቆጠራ ሂደቱ እንዲሁም የምርጫው ውጤት ትክክለኛ ስለመሆኑ በቃለ-ጉባዔ ተይዞ በፊርማ መረጋገጥ አለበት፡፡

4.3.4. ከየምድቡ ከፍተኛ ድምፅ ያገኙት ዕጩዎች በዳይሬክተርነት የሚሾሙ ሲሆን፤ የተቀሩት ደግሞ በየምድባቸው በያዙት ድምፅ ቅደም ተከተል በተጠባባቂነት ይያዛሉ።

4.3.5. የድምፅ ቆጠራው ውጤት ድምፅ በተሰጠበት ቀን ለጠቅላላ ጉባኤው ይገለጻል፡፡ ይህን ማድረግ የማይቻል ከሆነ ግን በቀጣዩ የሥራ ቀን በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት የማስታወቂያ ሰሌዳ እና በባንኩ ድህረ ገጽ ላይ መለጠፍ አለበት፡፡

4.3.6. በባንኩ የባለአክስዮኖች መዝገብ ውስጥ ተፅዕኖ ፈጣሪ ባለአክስዮን ከሌለ የቦርዱ ምርጫው ሁሉም ባለአክስዮኖች በሚሰጥ ድምፅ መሰረት ይካሄዳል።

ክፍል አምስት

የቦርድ አባላት ሹመት ስለ ማስፀደቅ

5.1. የቦርድ አባላት ሹመት መፅደቅ

በምርጫ ከፍተኛ ድምፅ አግኝተው ያለፉ የቦርድ ዳይሬክተሮች ሹመት የሚፀድቀው በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፀድቆ በሰነዶች ምዝገባ እና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ሲመዘገብ ይሆናል።

5.2. የተጓደሉ የቦርድ አባላት ስለመተካት

5.2.1. ዳይሬክተሮች በተለያየ ምክንያት በቦርድ ላይ ያላቸውን መቀመጫ የለቀቁ እንደሆኑ ከየምድቡ በተጠባባቂነት ዝርዝር ውስጥ የሰፈሩ አባላት ባላቸው የድምፅ ቅደም ተከተል መሰረት በዳይሬክተርነት ይሾማሉ።

5.2.2. ለገለልተኛ አባላት የተሰጡ መቀመጫዎች በምንም አይነት መልኩ ገለልተኛ ላልሆኑ አባላት ሊተላለፉ አይችሉም።

5.2.3. የተተኪ ሴቶችን ተሳትፎ ለማረጋገጥ በተቻለ መጠን በተጠባባቂዎች ዝርዝር ውስጥ ሴቶች የሚካተቱበት ሁኔታ መፈጠር ይመረጣል።

5.3. በህግ ስልጣን ባላቸው አካላት አማካይነት ስለሚደረግ የቦርድ አባላት ምርጫ

5.3.1. ብሔራዊ ባንክ የቦርድ ምርጫ እንዲካሄድ ከወሰነ፣ ሒደቱ የሚካሄደው የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2008 (በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1159/2019) ንዑስ አንቀጽ 12 (1) (ለ) እና (2) መሠረት ይሆናል።

5.3.2. በፍርድ ቤት፣ የውጭ አዲተሮች ወይም በህግ ስልጣን ባለው አካል ትእዛዝ የቦርድ ምርጫ እንዲካሄድ ሲወሰን የምርጫ ሂደቱ አግባብ ባላቸው ህጎች መሰረት የሚከናወን ይሆናል።

5.4. ማሻሻያ

ይህ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የጥቆማ እና የምርጫ አፈጻጸም ፖሊሲ እና መመሪያ በጠቅላላ ጉባዔው ሊሻሻል ይችላል።

5.5. ተፈጻሚነት

ይህ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የጥቆማ እና የምርጫ አፈጻጸም ፖሊሲ እና መመሪያ ህዳር 28 ቀን 2017 ዓ.ም ለማህበሩ 20ኛ የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ በሙሉ ድምፅ የፀደቀ ሲሆን፤ በሚመለከተው መዝጋቢ አካል ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

==========//==========